# መመሪያ ቁጥር 899/2014

# የሀይማኖት ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ፈቃድ አሠጣጥ መመሪያ

የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

ግንቦት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 899/2014

## የሀይማኖት ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ፈቃድ አሠጣጥ መመሪያ

በሳተላይት ወይም በኬብል አማካኝነት የሚሰራጭ የሃይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት የሃይማኖት ተቋማት አስተምህሮታቸውን በብሮድካስት ጣቢያዎች ለማድረስ እንዲሁም በማህበራዊ ጉዳዮች፣ በሠላም ግንባታ፣ በሥነ-ምግባር ዕሴቶች፣ በታሪክ እና መሰል ሃይማኖታዊ እሴቶች ዙሪያ ማሕበረሰቡን ለማስተማር፤ ህብረተሰቡም ባለበት ቦታ ሆኖ ሃይማኖታዊ ፕሮግራሞችን ለመከታተል እንዲችል፤ የሃይማኖት ብሮድካስት ጣቢያዎችም ሃይማኖታዊ ሚናቸውን በተገቢው መንገድ እንዲጫወቱ ለማስቻል፤

የሃይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ ሂደትን ግልጽ እና ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 6(1)፣(5) እና 40(3)(ለ)፤ መሰረት የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አመልካቾች ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም ባለፈቃዶች ሕገ መንግስቱን፣ የአገሪቱን ሕጎች እንዲሁም፤ የሕዝብን ሰላም፣ ደኅንነት፣ የዜጎችን ተነፃፃሪ መብቶችና ጥቅሞች ባከበረ መልኩ በኃላፊነት ስሜት ሥራቸውን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 12(7) እና አንቀፅ 90(2) መሰረት ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የሀይማኖት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፈቃድ አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 899/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ***ትርጓሜ***

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ ***"የሃይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት"*** ማለት፡-

ሀ) በሕግ ወይም በሠላም ሚኒስቴር ወይም የሃይማኖት ተቋማትን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ተመዝግቦ ዕውቅና ባገኘ የሃይማኖት ተቋም፤ ወይም

ለ) የሃይማኖት ድርጅቶችን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ወይም በሠላም ሚኒስቴር የሃይማኖት ብሮድካስት እንዲያቋቁም ተፈቅዶለት ወይም ተመዝግቦ ዕውቅና ያገኘ ሃይማኖታዊ ማህበር፣ ሚኒስትሪ ወይም ሃይማኖታዊ ድርጅት ወይም መሰል በሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል የሚቋቋም፤ ወይም

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውጪ ቢሆንም፤ የሃይማኖት ብሮድካስት እንዲያቋቁም በልዩ ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተፈቀደለት አካል መሆኑ፤

መ) ትኩረቱን በሃይማኖታዊ ጉዳይ፣ በማህበራዊ ጉዳይ፣ በሠላም ግንባታ፣ በሥነ-ምግባር ዕሴቶች፣ በታሪክ እና መሰል ሃይማኖታዊ እሴት ላይ ያደረገ፤ እና

ሠ) በሳተላይት ወይም በኬብል አማካኝነት የሚሰራጭ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

2/ ***"የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት"*** ማለት በኬብል ወይም በሳተላይት ማሰራጫዎች አማካኝነት የሚተላለፍ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው፡፡

3/ ***"የፈቃድ አመልካች"*** ማለት የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ ሰው ነው፤

4/ ***"የሀይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃድ"*** ማለት በመገናኛ ብዙሃን አዋጅና በዚህ መመሪያ መሠረት የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት ከባለሥልጣኑ የሃይማኖት ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ፈቃድ የተሰጠው ባለፈቃድ ነው፤

5/ ***"የሳተላይት ብሮድካስት አገልግሎት"*** ማለት ሳተላይት ላይ በተቀመጡ ማሰራጫዎች አማካይነት የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡

6/ ***"የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል"*** ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ተቀብሎ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ መደበኛ የሥራ ክፍል ነው፡፡

7/ ***"ፕሮግራም ኃላፊ"*** ማለት በሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ያለው የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

8/ ***"የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ"*** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

9/ ***"የሃይማኖት ብሮድካስት ድርጅቶች የጋራ ማህበር"*** ማለት የርስ በርስ አቅም ግንባታ፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በሃይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃዶች የጋራ ሥምምነት የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡

10/ ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፡፡

11/ ***"ቦርድ"*** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፡፡

12/ ***"አዋጅ"*** ማለት የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ነው፡፡

13/ ***"ሰው"*** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም ማህበር ነው፡፡

14/ የሃይማኖት ድርጅቶችን በተመለከተ በሌሎች አዋጆች የተሰጡ ትርጉሞች እንደአግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

15/ በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ የሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. *<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>*

ይህ መመሪያ በሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ሰጪ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. *<u>የመመሪያው አላማዎችና መርሆች</u>*

1/ ይህ መመሪያ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) ሃይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ሠጪ ፈቃድ በማግኘት እንዲንቀሳቀስ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

ለ) የሃይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ሠጪዎች ሕገመንግስቱን፣ የአገሪቱን ሕጎች፣ የሃይማኖቶችን እኩልነት እንዲሁም የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም አክብረው መስራታቸውን ማረጋገጥ፡፡

2/ ይህ መመሪያ በሚከተሉት መርሆች ይመራል፤

ሀ) ልዩነቶችን በማክበር በሠላም አብሮ መኖርን የሚያበረታታ፤

ለ) በመንግስትና በሃይማኖቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ርቀት ማስከበር፤

ሐ) በሃይማኖት ብሮድካስት የሚሰራጩ ይዘቶች ለፖለቲካ አላማ አለማዋላቸውን ማረጋገጥ፤

## *ክፍል ሁለት*

## *የሀይማኖት ሬዲዮና ቴሌቪዥን የፈቃድ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሂደት*

### 5. *አጠቃላይ*

1/ የሀይማኖት ብሮድካስት ፈቃድ የሚሰጠው፡-

ሀ) በሕግ ወይም በሠላም ሚኒስቴር ወይም የሃይማኖት ተቋማትን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ተመዝግቦ ዕውቅናና የሕግ ሰውነት ለተሰጠው የሃይማኖት ተቋም፤

ለ) የሃይማኖት ተቋም ካልሆነም፤ የሃይማኖት ድርጅቶችን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ወይም በሠላም ሚኒስቴር የሃይማኖት ብሮድካስት እንዲያቋቁም ተፈቅዶለት ወይም ተመዝግቦ ዕውቅና ባገኘ ሃይማኖታዊ ማህበር፣ ሚኒስትሪ ወይም ሃይማኖታዊ ድርጅት፣ ወይም መሠል የሕግ ሰውነት ለተሠጠው አካል ሲሆን፤ እንዲሁም

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውጪ ቢሆንም፤ የሃይማኖት ብሮድካስት እንዲያቋቁም በልዩ ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተፈቀደለት አካል፤ ሲሆን

መ) የሃይማኖት ብሮድካስት ፈቃድ ለማግኘት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) መሰረት የሚያመለክት ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም ከሃይማኖት ተቋሙ የተፃፈ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፤

ሠ) የሃይማኖት ብሮድካስት ፈቃድ ለማግኘት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ለ) መሰረት የሚያመለክት ማንኛውም አካል፤ የሃይማኖት ብሮድካስት ለማቋቋም ከሠላም ሚኒስቴር ወይም የሃይማኖት ተቋማትን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው የሚመለከተው አካል የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል።

2/ ባለሥልጣኑ በሳተላይት ወይም በኬብል አማካኝነት ለሚሰራጭ የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾች ያለውድድር በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ አመልካቹ መስፈርቱን ሙሉ በሙሉ አሟልቶ ከቀረበ ባለስልጣኑ ቢበዛ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ፈቃድ መስጠት ይኖርበታል፡፡

4/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የሃይማኖት ብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም በታገደ ወይም በተሰረዘ ፈቃድ፡-

ሀ) የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶችን ተጠቅሞ በሀይማኖት የሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 29 ከተዘረዘሩት የብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ መንገዶች መካከል ቀደም ሲል ፈቃድ ካገኘበት የፈቃድ አይነት ውጪ ከባለሥልጣኑ ሌላ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይሰጠው የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

## 6. <u>ስለፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ</u>

1/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፤ የማመልከቻ ቅፆችንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ እንዲሞሉ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

ሀ) የአመልካቹ ወይም የሃይማኖት ተቋሙ ወይም የጣቢያው መጠሪያ ስምና አድራሻ፣

ለ) የብሮድካስት አገልግሎቱ ዓላማ፣ የሚሰራጭበት ቋንቋ፣ የሥርጭት ቀን፣ ሰአትና አጠቃላይ ሁኔታ፣

ሐ) ለስርጭቱ የሚውለውን የመሣሪያ አይነትና ጉልበት፣

መ) አገልግሎቱ የሚሰጥበትን፣ የማሰራጫ መሳሪያው የሚተከልበትን ወይም የሚቋቋምበትን ቦታ፣

ሠ) ጣቢያውን ለማቋቋምና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገውን የገንዘብና የካፒታል መጠንና ምንጭ፣

ረ) የሚጠቀምበትን የሳተላይት መጠሪያ ስም፣ የሳተላይት አከራዩ ባለቤት ስም፣ አድራሻ፣ መሰል መረጃ፣

ሰ) ሌሎች አገልግሎቱን እና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎችን፡፡

2/ አመልካቹ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ማቅረብ ይኖርበታል።

7. <u>*ከማመልከቻ ቅፅ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች*</u>

አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች በማሟላት ከማመልከቻ ቅፁ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1/ አመልካቹ የሀይማኖት ድርጅት ከሆነ፤ በሕግ ወይም በሠላም ሚኒስቴር ወይም የሃይማኖት ተቋማትን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ተመዝግቦ ዕውቅናና የሕግ ሰውነት የተሰጠው የሃይማኖት ተቋም መሆኑን የሚያስረዳ ሠነድ፣ እንዲሁም ከሃይማኖት ተቋሙ የተፃፈ ደብዳቤ፤

2/ አመልካቹ የሀይማኖት ድርጅት ካልሆነ፤ የሃይማኖት ድርጅቶችን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ወይም በሠላም ሚኒስቴር የሃይማኖት ብሮድካስት ለማቋቋም የተፈቀደለት ወይም የተመዘገበ ሃይማኖታዊ ማህበር፣ ድርጅት ወይም ሚኒስትሪ ወይም መሠል የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል መሆኑን የሚያስረዳ ሠነድ፤ እንዲሁም የሃይማኖት ብሮድካስት ለማቋቋም የተሠጠውን የድጋፍ ደብዳቤ፤

3/ አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውጪ ከሆነም፤ የሃይማኖት ብሮድካስት ለማቋቋም በባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው አስፈላጊ ሠነድ፤

4/ የፕሮግራሙን አላማ፣ የአገልግሎትና የቴክኒክ ሁኔታን የሚገልፅ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ፣

5/ ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልግ የገንዘብና የካፒታል አቅምና ምንጭ የሚያስረዳ ማንኛውም አይነት ሰነድ ወይም ፕሮፖዛል፣ የድጋፍ ሰነድ፣

6/ የጣቢያው ድርጅታዊ መዋቅር ሰነድ፣

7/ የጣቢያውን ሥራ የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎች፣ የፕሮግራም ኃላፊዎችና የባለሙያዎች የሰው ሀይል ዝርዝር፣ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

8/ አገልግሎቱ የሚሰጥበትን ቦታ አድራሻ፣ የማሰራጫ መሳሪያ የሚገኝበት መልክአምድራዊ መረጃ፣

9/ የብሮድካስት አገልግሎቱ ዓላማ፣ የፕሮግራሙን አይነት፣ የሚሰራጭበት አገራዊ ቋንቋ ብዛት፣ የሥርጭት ቀን፣ ሰአትና አጠቃላይ ሁኔታ፣ የሚያስረዳ ሰነድ፣

10/ ፕሮግራሙ የሚሰራጭበት ሳተላይት ስም፤ የፍሪኩዌንሲ መጠሪያ ቁጥር፣

11/ ሌሎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎትንና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎች፡፡

8. ***<u>የፈቃድ መስጫ አጠቃላይ መስፈርቶች</u>***

የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካትታል፡፡

1/ አመልካቹ በሕግ ወይም በሠላም ሚኒስቴር ወይም የሃይማኖት ተቋማትን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ተመዝግቦ ዕውቅናና የህግ ሰውነት ያገኘ የሃይማኖት ድርጅት መሆኑ፤እንዲሁም ከሃይማኖት ተቋሙ የተፃፈ ደብዳቤ መኖሩ፤

2/ አመልካቹ የሃይማኖት ድርጅት ካልሆነ የሃይማኖት ድርጅቶችን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ወይም በሠላም ሚኒስቴር የሃይማኖት ብሮድካስት እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ወይም የተመዘገበ ሃይማኖታዊ ማህበር፣ ድርጅት ወይም ሚኒስትሪ ወይም መሠል የሕግ

ሰውነት የተሰጠው አካል መሆኑ፤ እንዲሁም የሃይማኖት ብሮድካስት እንዲያቋቁም የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ መኖሩ፤

3/ አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውጪ ከሆነ፤ የሃይማኖት ብሮድካስት ለማቋቋም በልዩ ሁኔታ እንዲፈቀድለት ለባለሥልጣኑ ያቀረባቸው ሠነዶች ተቀባይነት፣

4/ የፋይናንስ አቅምና ምንጭ ሥራውን ለማስኬድ ያለው ዝግጁነት፤

5/ የብሮድካስት አገልግሎቱ ወይም የፕሮግራሙ አላማ፣ የሥርጭት ቀንና ሰአት፤

6/ በአመልካቹ ፕሮጀክት ሀሳበ-ሥራ የተዘረዘሩት መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት በቂ መሆኑ፤

7/ በአዋጁ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ፈቃድ ከማይሰጠው ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፤

9. ***<u>የፈቃድ መስጫ ዝርዝር መስፈርቶች እና የመገምገሚያ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት</u>***

ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 የተዘረዘሩትን አጠቃላይ የፈቃድ መስፈርቶች መሠረት በማድረግ የአመልካቾችን ብቃት በመመዘን ነጥብ ለመስጠት የሚያስችለውን ዝርዝር መስፈርት እና የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት ሠነድ ያዘጋጃል፤ በባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማስፀደቅ ስራ ላይ ያውላል፡፡

10. ***<u>የሀይማኖት ብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሂደት</u>***

የሀይማኖት ብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርአት ሂደት የሚከተለውን የሥራ ፍሰት ጠብቆ ይከናወናል፡-

1/ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚፈልግ አመልካች በማናቸውም ጊዜ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ከደጋፊ ሠነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ያቀርባል፤

2/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመርና የመጀመሪያ ማጣሪያ በማድረግ፡-

ሀ) አመልካቹ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፣ ወይም በአዋጁ በአንቀጽ 40 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው አካል መሆኑን ካረጋገጠ፣ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆንና ውሳኔው ለአመልካቹ በጽሁፍ እንዲገለፅለት የውሳኔ ሃሳቡን ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

ለ) አመልካቹ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካቀረበና በአዋጁ በአንቀጽ 40 መሠረት ፈቃድ ሊሰጠው የሚችል አካል መሆኑን ካረጋገጠ፣ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 እና 9 የተዘረዘሩት የፈቃድ መስፈርቶች መሚላታቸውን ለማረጋገጥና ለመመዘን ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ እንዲያልፍ ውጤቱን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

3/ የበላይ ሃላፊው ከፈቃድ ስራ ክፍሉ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ በመመርመርና ወደ ሁለተኛ ማጣርያ እንዲያልፍ በማፅደቅ ምዘናና ግምገማ እንዲካሄድ ይወስናል፡፡

4/ የፈቃድ ስራ ክፍሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የቀረበለትን ማመልከቻ በአንቀጽ 7 እና 8 የተዘረዘሩትን ሰነዶችና መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ፣ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9 መሰረት በተዘጋጀው የፈቃድ አሰጣጥ የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ የአሰራር ሥነ ሥርአት መሰረት የአመልካቹን ብቃት በመመዘን አመልካቹ ያገኘውን ውጤት የያዘ የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

5/ የበላይ ኃላፊው የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት መርምሮ አመልካቹ የፈቃድ መስጫ መስፈርቶችን ማሟላቱን ሲያረጋገጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6/ አመልካቹ መስፈርቱን አለማሟላቱ ከተረጋገጠ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኝ በማድረግ መስፈርቱን የሚያሟላበት ሁኔታ ይመቻቻል፣ መስፈርቱን ለማሟላት ካልቻለም የፈቃድ ማመልከቻው ይሰረዛል፡፡

7/ የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታን የያዘ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ከፈረመና ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ ከከፈለ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

8/ የፈቃድ ምስክር ወረቀት እንዲወስድ በጽሑፍ የተገለፀለት አመልካች ደብዳቤ በደረሰው በ2 ወር ጊዜ ውስጥ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ካልወሰደ የፈቃድ ውሣኔው ይሰረዛል፡፡

11. ***የሀይማኖት ብሮድካስት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመንና ስለፈቃድ እድሳት***

1/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን 10 አመት ይሆናል፡፡

2/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተወሰነው 10 አመት የፈቃድ ዘመን ከመጠናቀቁ ከ6 ወራት በፊት ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማሳደሻ ቅጽ ሞልቶ ማመልከቻውን በማቅረብ ፈቃዱን ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የታደሰ ፈቃድ በየ2 አመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

4/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍል ፈቃዱን ከማደሱ በፊት፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን፣ በአዋጁ፣ ደንብና መመሪያዎች የተመለከቱ ግዴታዎች የማክበር የኋላ ታሪክና የተወሰዱበት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አለመኖራቸውን ከግምት ውስጥ ማስገባት፣

ለ) ባለፈቃዱ በሠላም ሚኒስቴር፣ የሃይማኖት ተቋማትን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ወይም በሃይማኖት ብሮድካስት ተቋማት የጋራ ምክር ቤት የቀረበ ተደጋጋሚ የሆነ የቅሬታ ሪከርድ የሌለበት መሆኑን ወይም ምክረ ሃሳብ ከግምት በማስገባት፤ እንዲሁም

ሐ) በባለሥልጣኑ የሞኒተሪንግና ክትትል ውጤት ተደጋጋሚ ግድፈት ያልተገኘበት መሆኑን፣ እንዲሁም

መ) ባለፈቃዱ በፈቃድ ዘመኑ ውስጥ አመታዊ ክፍያውን በወቅቱ ይከፍል የነበረ መሆኑን በማረጋገጥ ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

5/ የበላይ ኃላፊው የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና መረጃዎች መርምሮ ፈቃድ እንዲታደስ ወይም እንዲሰረዝ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የውሳኑ ሃሳብ በመገምገም የአመልካቹን ፈቃድ የማያድስ ከሆነ ከ3 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

6/ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ለፈቃድ እድሳት የተተመነውን ክፍያ ከፍሎ የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ያገኛል፡፡

12. ***ተቀባይነት ስላላገኘ የፈቃድ እና የእድሳት ማመልከቻ***

1/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) በአንቀፅ 10(2)(ሀ)፣ 10(8) እና 11(5) መሰረት የፈቃድ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ወይም እንዲሰረዝ ውሳኔ ከሰጠ፤ ማመልከቻው ውድቅ የሆነበትን ወይም የተሰረዘበትን ምክንያት በ14 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅና ቅሬታ ካለውም በፅሁፍ እንዲያቀርብ እድል መስጠት ይኖርበታል፡፡

2/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በበላይ ኃላፊው ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

3/ ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና የውሳኔውን ቅጂም በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

4/ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

13. ***የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች***

1/ ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚከተሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች ያካተተ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ያዘጋጃል፤ የፈቃድ ሥምምነት ሰነዱን አመልካቹ እንዲያገኛቸውና አስተያየቱን የመግለፅ እድል እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡

ሀ) የቴክኒክ መስፈርቶች፤

ለ) የብሮድካስት አገልግሎቱ ሥርጭት የሚጀምርበት ጊዜ፣

ሐ) ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜና የፈቃድ ማደሻ ሁኔታዎች፤

መ) የአገልግሎት ክፍያ መጠን፤

ሠ) የፕሮግራምና የይዘት ህጋዊነት፣ ደረጃዎች፤

ረ) ባለሥልጣኑ በአዋጁና በመመሪያው መሰረት እንዲቀርቡ የሚጠይቃቸው ሠነዶች፤

ሰ) ፈቃድ የሚሻሻልባቸው ሁኔታዎች፤ እና፣

ቀ) ቅሬታዎችና አለመግባባቶች የሚስተናገዱበት መንገድ፤

2/ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው ላይ የገለፀው የፈቃድ ሁኔታና የፈቃድ ስምምነት ሠነድ የፈቃድ ግዴታዎች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡

## *ክፍል ሦስት*

## *የሃይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃድ መብቶችና ግዴታዎች*

### 14. *የሀይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃድ መብቶች*

1/ ሃይማኖታዊ አስተምሮታቸውን፣ የፀሎት መርሃ ግብሮቻቸውን፣ ማህበራዊ ጉዳዮችን የማከናወን፣ በሠላም ግንባታና በስነ ምግባር የማነፅና የማስተማር፣ ሃይማኖታዊ ተግባራቸውን በነፃነት የሚያራምዱበትን ምህዳር የመፍጠር እና ለሃይማኖቱ ተከታዮቻቸው ተደራሽ የመሆን መብት አላቸው፡፡

2/ ተግባራቸውን በብቃት ለመፈጸም በሚያስችላቸው ሁኔታ በይዘት፣ በአደረጃጀታቸውና በበጀታቸው ከመንግሥት አካላት እና ከፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች ነፃ የመሆን መብት አላቸው፡፡

3/ ኤዲቶሪያል ነፃነት የተጠበቀ ነው፤ በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ ነው፡፡

4/ በሕግ በግልፅ ከተመለከተው አግባብ ውጪ በብሮድካስት ስርጭት ላይ የይዘት ግዴታዎች አይጣሉም፡፡

5/ የሃይማኖት ባለፈቃዶች በመረጡት ሕጋዊ መንገድ የመደራጀት መብት አላቸው፡፡

6/ በአዋጁ አንቀፅ 49 ከተመለከተው ውጪ ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡

7/ በዚህ መመርያ በግልፅ የተመለከቱ መስፈርቶችን በማሟላት ፈቃድ የማግኘት፣ የፈቃድ እድሳትና ሌሎች ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ድጋፎችን የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

8/ የሃይማት ብሮድካስት አገልግሎቱን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ከሃይማኖቱ ማህበረሰብ የገንዘብና ማቴርያል ድጋፍ የመጠየቅ፡፡

15. ***ፕሮግራም እና ማስታወቂያን በሕግ አግባብ ስለማሰራጨት***

1/ በሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ኘሮግራም የሚከተሉትን ማክበር ይኖርበታል፡-

ሀ) ሕገ መንግስቱን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁን እና ሌሎች የአገሪቱን ሕጎች ማክበር ይኖርበታል፤

ለ) በኃይማኖቶች ተከታዮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት ማነሳሳት፣ የሌሎችን ሀይማኖታዊ አስተምሮ ወይም እምነት ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ማንኳስስ ወይም በሀይማኖቶች ተከታዮች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር መቀሰቅስ፣ ወይም የሃይማኖት እኩልነትን መፃረር የለበትም፡፡

ሐ) ማንኛውም የሰው ዘርን፣ ቋንቋን፣ ብሔርን፣ ኃይማኖትን ወዘተ መሰረት በማድረግ የወንጀል ድርጊት እንዲፈጸም፣ ሰላምና ፀጥታ እንዲደፈርስ መቀስቀስ የለበትም፣

መ) ከማህበረሰቡ ባህልና ሥነ ምግባር የተቃረነ፤ የማህበረሰቡን ጤና የሚጎዳ፣ ማህበረሰቡን በሀሰት የሚያሳስት ይዘት ማሰራጨት የለበትምት፣

2/ የሃይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃድ፡-

ሀ) ለሁሉም ሀይማኖቶችና እምነቶች ተገቢ ክብር እንደተሰጣቸው ሊያረጋግጥና የሀይማኖትና የእምነት ነጻነትንና መሰረታዊ ሰብዓዊ መብትን ሊጠብቅ ይገባል፡፡

ለ) ማንኛውንም ፕሮግራም በጣቢያው ከማሠራጨቱ በፊት ፕሮግራሙ እውነተኛና ሕግን የሚያከብር መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ስህተት ሲገኝም ማረም አለበት፡፡

ሐ) ማንኛውም የንግድ ማስታወቂያና የስፖንሰር ሽፕ መግለጫ ከመሠራጨቱ በፊት የማስታወቂያ ሕግን የሚያከብር መሆኑን ማረጋገጥ እና የማስታወቂያ ምጣኔውም ከአንድ ፕሮግራም ወይም ከዕለቱ የሥርጭት ጊዜ ከ7 በመቶ የማይበልጥ መሆኑን ማረጋገጥ ኖርበታል፡፡

16. ***የሀይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃዱ አስተዳደራዊ ግዴታዎች***

*የሀይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ተግባር፣ ሃላፊነቶች መከናወናቸውን ያረጋግጣል፡-*

1/ ለሚያስመጣቸው መሳሪያዎች በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የማረጋገጫ ሠርተፍኬት የማግኘት፣

2/ በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የፕሮግራም "ቻናል" ብቻ ፕሮግራሙን የማሠራጨት፤

3/ ጣቢያው በአገር ውስጥ የሚቀጥራቸው ባለሙያዎች የውጭ አገር ዜጐች ከሆኑ በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል የስራ ፈቃድ ያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ፣

4/ በጣቢያው ሥርጭት የጣቢያውን ስያሜና ምልክት የመግለጽ፤

5/ በጣቢያው የፕሮግራም ኃላፊ አድርጎ የሚመድበውን ሰው ስም ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፤

6/ ያሰራጨውን ማናቸውም ፕሮግራም ለ30 ቀናት ቀርፆ የመያዝ፤ በተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበም ባለፈቃዱ ቅሬታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ፕሮግራሙን ቀርጸ ማስቀመጥ፤ ቅጅውን እንዲያቀርብ ሲጠይቅም በራሱ ወጪ የማቅረብ፤

## 17. *ለውጦችን ስለማሳወቅና ስለማስፈቀድ*

1/ የሀይማኖት ብሮድካስተሩ የሚከተሉትን ለውጦች ባደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲጀመርና ሲቋረጥ፤

ለ) የጣቢያው ስም፣ ምልክትና አድራሻ ላይ ለውጥ ሲያደርግ፤

ሐ) የጣቢያው ሥራ አስኪያጅና የፕሮግራም ኃላፊ ሲለውጥ፤

መ) ፈቃድ ለመውሰድ ባቀረባቸው ወይም በተፈቀደለት የብሮድካስት የማሠራጫ መሣሪያ አይነት ወይም ሌሎች ጉዳዮችና መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያደርግ፣

2/ ባለሥልጣኑ የተደረገው ለውጥ በሕግ አግባብ መከናወኑን ይገመግማል፡፡

## 18. *እርማት ወይም መልስ የመስጠት ግዴታ*

1/ በሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት በተላለፈ ፕሮግራም መብቴ ተነክቷል ወይም ፕሮግራሙ በአግባቡ አልቀረበም በማለት ቅሬታውን ለጣቢያው የሚያቀርብ ሰው ሲኖር፤ ባለፈቃዱ የቅሬታ አቅራቢውን መብት ሊያከብርለት እና ለጣቢያው የሚያቀርበውን እርማት በፅሁፍ በደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ በተመጣጣኝና በተመሳሳይ የአየር ጊዜ ያለ ክፍያ ሊያስተላልፍለት ይገባል፡፡

2/ ጣቢያው እርማቱን ለማስተላለፍ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ካመነበትም ከ3 ሳምንት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ እርማቱን ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን የዘገየበትን ምክንያትም በስልክ ወይም በደብዳቤ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት።

3/ እርማት የማውጣት ወይም መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ሰው ጣቢያው ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ወይም ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡

19. ***ጥቆማ፣ ቅሬታንና ግብረ መልስን ስለማስተናገድ***

1/ ባለፈቃዱ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥነ ሥርዓት በመዘርጋት ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብ ጥቆማ እና ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡

2/ ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ ለሚቀርብለት ግብረ መልስ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የወሰደውን ማስተካከያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3/ ባለፈቃዱ ከሚሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት ጋር በተያያዘ በማናቸውም ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ከተወሰነበት የአቤቱታውን ብዛት፣ ምክንያት፣ የተሰጠውን ውሳኔና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

20. ***የብሮድካስት አገልግሎት ክፍያዎችን ስለመክፈል***

1/ የሀይማኖት ብሮድካስት ባለፈቃድ የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ፣ የፈቃድ ክፍያ እና የፈቃድ ማደሻ ክፍያውን ለማህበረሰብ ሬዲዮ በተተመነው የክፍያ ተመን መሰረት ይከፍላል፡፡

2/ የክፍያው መጠን በባለስልጣኑ በየጊዜው እየተጠና በመንግስት በሚጸድቅ ተመን መሰረት ሊለወጥ ይችላል፡፡

## ***ክፍል አራት***

## ***ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች***

21. ***የባለሥልጣኑ ተግባርና ሃላፊነት***

ባለሥልጣኑ፡-

1/ መገናኛ ብዙሃን ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀላሉ፣ በቀጥታና ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ሠጪውን ስም፣ አድራሻ፤ የፖስታና የስልክ ቁጥር፣ የኢሜልና የድረ-ገፅ አድራሻ፣ የጣቢያውን ስራ አስኪያጅና ተወካዮች ስምና ስልክ ቁጥር በማጠናቀርና በመመዝገብ በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ ተደራሽ ያደርጋል፣

2/ በሃይማኖት ብሮድካስት የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትል እና የድጋፍ ስራዎችን ከሃይማኖት ብሮድካስተሮች የጋራ ማህበር፣ ከሃይማኖት ድርጅቶች፣

ከሠላም ሚኒስቴር፣ የሃይማኖት ተቋማትን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው የሚመለከተው አካልና ማህበር ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

3/ በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ያረጋግጣል፡፡

4/ በቦርዱ የፀደቁ መመሪያዎችን አሳትሞ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፡፡

22. ***የመሸጋገሪያ ድንጋጌ***

አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በስርጭት ላይ የሚገኙ የሀይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ሰጪዎች በአዋጁና በመመሪው መሰረት ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

23. ***መመሪያውን ስለማሻሻል***

የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል::

24. ***የአዋጁ ተፈጻሚነጽና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች***

1/ ከሃይማኖት ብሮድካስት ጋር በተያያዘ በአዋጅ የተመለከቱት ሌሎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

25. ***መመሪያው የፀና ስለመሆኑ***

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ የሥራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ከግንቦት 9 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

***የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን የሥራ አመራር ቦርድ***